OM KLÆR I BARNEHAGEN
**AMHARISK**

# በመዋዕለ ሕፃናት ውስጥ የሚያስፈልጉ አልባሳት



### አልባሳት

መዋዕለ ሕፃናት ውስጥ ህፃኑ የሚለብሰው ልብስ ቢቆሽሽ ወይም ቢበላሽ የማያሳስቦት ዓይነት መሆን አለበት። ልብሶቹ ለማልበስና ለማውለቅ የማያስቸግሩ፣ ለሕፃኑ እንቅስቃሴ ምቹ የሆኑ መሆን አለባቸው። በርገን ብዙ ዝናብና ተለዋዋጭ የአየር ሁኔታ ስላለ፣ ሕፃናትን ትክክለኛ ልብስ ማልበስ አስቸጋሪ ሊሆን ይችላል። ሕፃናቱ ሊበርዳቸው አይገባም። ሆኖም ግን ሕጻናት ንቁና ቀልጣፋ ስለሆኑ የሚደራርቡት ልብስ በዝቶባቸው ጨዋታና እንቅስቃሴያቸዉን ማደናቀፍ የለበትም።  ለተለያዩ የአየር ጠባዮች ተስማሚ የሆኑ ልብሶችን በመምረጥ ረገድ የመዋዕለ ሕፃናቱ ሠራተኞች ሊያግዟችሁ ይችላሉ።

## በልብሶች ላይ ምልክት ማድረግ

ህፃኑ ወደ ቤቱ ሲሄድ ትክክለኛውን ልብስ ለመያዙ እርግጠኛ ለመሆን፥ ሁሉም ልብሶች ስም ቢጻፍባቸው ጥሩ ይሆናል።  በልብሶች በውስጥ በኩል የሚለጠፉ የስም ባጆችን በኢንተርኔት ማዘዝ ይቻላል። በውሃ  በማይለቅ ቀለም ልብሶቹ ላይ መለያ ምልክት ማድረግም ይቻላል።

### ሕፃናቱ በመዋዕለ ሕፃናት ውስጥ ምን ዓይነት ልብስ ያስፈልጋቸዋል?

ዝናብ ሲዘንብ እና ውጪው እርጥብ ሲሆን ሕፃናቱ የዝናብ ልብስ እና ቦት ጫማ ያስፈልጋቸዋል። የዝናብ ልብስ በመዋዕለ ሕፃናቱ ውስጥ በቋሚነት ማስቀመጥ ጠቀሜታ አለው። የዝናብ ልብሶቹ ሲቆሽሹ ወደ ቤት ተወስደው መታጠብ ይኖርባቸዋል።

ሕፃናቱ በየቀኑ የሚጠቀሙበት የቤት ውስጥ ጫማ ወይም ነጠላ ጫማ ሊኖራቸው ይገባል። ወለሉ የሚያዳልጥ ሊሆን ስለሚችል ህፃናቱ በካልሲ የሚሄዱ ከሆነ ሊያዳልጣቸው ይችላል። ወለሎቹም እርጥበት ይኖርባቸውና ሕፃናቱ የቤት ውስጥ ጫማ ወይም ነጠላ ጫማ ባለማድረጋቸው እግሮቻቸው ሊረጥቡ ይችላሉ።












## ተጨማሪ ልብሶች

ህፃናት በመዋዕለ ህፃናቱ ውስጥ ሲጫወቱ መርጠባቸውና መቆሸሻቸው የተለመደ ነገር ነው። ይህ ሲሆን ልብሳቸውን መቀየር ይኖርባቸዋል። ስለዚህ በመዋዕለ ሕፃናቱ ውስጥ እንደ ግልገል ሱሪ (ፓንት)፣ ካልሲ፣ ረጅም ካልሲ፣ ሹራቦችና ሱሪዎች የመሳሰሉ ተጨማሪ ልብሶች ማስቀመጥ በጣም አስፈላጊ ነው። ሕፃኑ የሚያስፈልጉት ተጨማሪ ልብሶች እንዳሉት በየጊዜው ያረጋግጡ።

## በበጋማው ግምሽ ዓመት

የአየሩ ሁኔታ ሞቃታማ ሲሆን ሕፃናቱ ቀለል ያለ ልብስና ጫማ ያስፈልጋቸዋል። በጸደይ እና በመኸር ወቅቶች ሳሳ ያሉ ቆቦች፣ እና የደጅ ቱታ (parkdress) ተስማሚ ናቸው። ውጪው ፀሃያማ በሚሆንበት ጊዜ፣ ጠንካራ የሆነ ከፀሃይ ብርሃን ጉዳት የሚከላከል ቅባት ይዘው መምጣት አለባቸው። በተጨማሪም ጭንቅላትን ለመከላከል የጸሀይ ቆብ ወይም ኮፍያ ቢኖራቸው ይመከራል።


© Trude Haugen



© Marte Rosenvinge

## በክረምታማው ግማሽ ዓመት

ውጪው ቀዝቃዛ ሲሆን፣ ሕጻናት ሙቀት የሚሰጥ የደጅ ቱታ ያስፈልጋቸዋል። በደጅ ቱታው ስር ከሱፍ ወይም ከበግ ጸጉር (ፍሊስ) የተሰራ ሹራብና ሱሪ መልበስ ይችላሉ። በተረፈ ሙቀት የሚሰጥ ቆብ፣ ከሱፍ የተሰሩ ካልሲዎች፣ ሙቀት የሚሰጡና ውሀ የማያስገቡ ጫማዎች፣ ሙቀት የሚሰጡ ድፍን ጓንቶች አስፈላጊ ናቸው። ድፍን ጓንቶች ስለሚረጥቡ በዛ ያሉ ተጨማሪ ጥንዶችን ማምጣትዎን ያስታውሱ።

## ህፃናቱ ውጪ በቆሙ ጋሪዎቻቸው ውስጥ ሲተኙ የሚኖራቸው አለባበስ

በእድሜ አነስተኛ የሆኑት ሕፃናት ቀን ላይ ማረፍ ይኖርባቸዋል። በአንዳንድ መዋዕለ ሕፃናት ውስጥ፣ ሠራተኞቹ እየጠበቋቸው ውጪ ጋሪዎቻቸው ውስጥ ይተኛሉ። በጋሪው ውስጥ የሚቀመጥ የመተኛ ቦርሳ ቢኖር፣ ሕጻኑ ብዙ ልብስ መደራረቡ ይቀርለታል።  የመተኛ ቦርሳ ውስጥ ሳሳ ያለ የሱፍ ልብስ ብቻ ማልበስ በቂ ሊሆን ይችላል። በክረምት ጊዜም ቢሆን። ጋሪ ውስጥ መተኛትን በተመለከተ መጠየቅ የሚፈልጉት ነገር ካለ የመዋዕለ ሕጻናቱን ሠራተኞች ያነጋግሩ።

## ሌሎች

የሽንት ጨርቅ (ፓምፐርስ), የጡጦ ጫፍ (smokk)፣ እንዲሁም እንዳስፈላጊነቱ የሕፃናት የእንክብካቤ ቅባት ለሚጠቀሙ ሕጻናት፣ እነዚህ ነገሮች የግዴታ በመዋዕለ ሕፃናቱ ውስጥ ሊቀመጡላቸው ይገባል።

---

BERGEN
KOMMUNE

Foto forside: © Nina Honningsvåg Træet
Skipnes.no Svanemerket trykksak, 2041 0731